ከነቦ ዉ.ቃዉ. ህዳር 12/2000

ኩዊንት-ዌስት/ኦንታሪኦ/ካናዳ

# “. . . አብረሕ አዝግም”

## (በርድስ ኦፍ ዘሴም ፌዘር፤ፍላይንግ ቱጌዘር)

“አይታክቱ ባንዶች ፤ታሪክ ይመርምሩ

የቆየ የቅድም ፤ያገሬ ልቦና፤ ለፋሺሰት ሲሰግድ ፤ለባንዳ ሲሳለም

አልታይቶም፤አልተሰምቶም፤አልተዋፎም”

*ፀጋዬ ገብረመድህን (ደብተራው) ቋራ 1977 ዓም*

ካያያዝ ይቀደዳል

ካነጋጋር ይፈረዳል

ሰው በሆዱ ይጮሀል

ሰው ለሆዱ ይጮሀል

ዘር ከልጓም ይስባል

በበላበት ይሰለፋል።

አንተማ ምን አጠፋህ?

ያለ ወግ-ያለ ማዕረግህ

ከፍ-ከፍ ያደረኩህ

ወርቅ ግዜ ያጠፋሁህብህ

አኔ ነኝ በርግጥ የዋህ

አንተማ ምን አጠፋህ?

የአገር ጉዳይ ከፊቴ እያለ

ወያኔ እየፏለለ

አገር እየገደለ

**ብዕሬ አለቦታው ሾለ።**

“ላቶ” አያቴን ምከሩ አለኝ!

አረ እንዴት ተሰለጠኝ!

“አሁን ምን ያረጋል ነገር መደጋገም

ባባት ያልሆነለት ባያት ምን ሊጠቀም”

ዕርባና የለሽ መናኛ

አባቱ ዳኛ፤ልጁ ቀማኛ

የማን ዘር ጎመን-ዘር

ተለቅላቂ፤አለቅላቂ

እርባና የሌለው እላቂ።

አይ የጫሪ ጥፉ

“ላሎቶ-አሎንሶ” ባንድ ተሰለፉ

በለፈለፉ ባፍ ይጠፉ

ይወለድ ዕና ዕንከፍ ዕንከፉ

ጋን ይሸከማል ዕስከ ድፍደፉ

አይ የጫሪ ጥፉ!።

#

የሰላቶ ልጅ ሰላቶ፤የፋሺስት የግራዚአኑ

መደየን ተራህ ነው ያባትህ ውጥኑ

ጋኖች አለቁ ና ምንቸቶች ጋን ሆኑ?

ባንድ ደንጊያ ሁለት ወፍ መምተት

አንዱ ደነዝ፤የቦዘበት

አንዱ ደናቁርት፤የዞረበት

የኔ ነው፤የኔ ነው፤ ጥፋት

ሳይሰጥ ደም ና ሽንት

ሳይመረመር የጀርባው አጥንት

የበሽታው፤ልኩ ጥናት

የዘር-ሐረጉ፤የደም-ልክፍት

ዱኒያው፤ቅሌት-ውርደት

የሌት-ሰቆቃው፤የቀን ቅዠት

ሲወረውረው-ወደ ላይ. . .

. . . ሲያጋጨው ከመሬት

እለኮሸሽላ፤አለብላቢት

“የፀጋዬ ብዕር፤ትንግርት”

“ኦቨር ዶዝ” ሆነበት::

መደዴዎቹን ፅሁፎች በ www.addisvoice.com እና በ www.abugida.com “ዉቃወ በደብተራ” በሚል ርዕስ ያገኟቸዋል

ቸር ይግጠመን